የካቲት 5-2002 ዓ.ም (12-2-2010)

# እራስን በራስ

በዚህ ዕርእስ በውጭ አገርና በአገር ውስጥ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ለማሳሰብና ብሎም ጥሪ ለማድረግ ሁኔታው አስገድዶኛል።ዝም ብሎ መመልከት ይቻላል ግን ዜግነቴ አልፈቀደልኝም። ስለሆነም በአለፉት ጊዜያት እንዳደረኩት ሁሉ በወቅታዊው ያገራችን ጉዳይ ላይ አሁንም ሃሳቤን ለማካፈል እወዳለሁ።ለማቀርበው ሃሳብ ተመሳሳይ አስተያየት ያላቸው ብዙ እንደሆኑ አምናለሁ።ይህ በብዙዎቹ አዕምሮ ውስጥ የሚሽከረከር ሃሳብ ወደ ተግባር ተተርጉሞ ውጤት እንዲሰጥ የመጀመሪያ የጥሪ ደወል በዚህ ጽሁፍ አማካኝነት ሳሰተላልፍ የሃሳቡ ደጋፊ አስፈላጊውን ትብብርና ተሳትፎ ያበረክታል ከሚል እምነት በመነሳት ነው።ከዳር ቆሞ ለምን እንዲህ አይደረግም ነበር ብሎ ከማለት ይልቅ እራስን አሳትፎ የሚችሉትን በማበርከት የማይፈልጉት ነገር እንዳይከሰት መከላከል ተገቢ ነው እላለሁ።

እንደሚታወቀው በአገራችን ውስጥ በሚካሄደው የፖለቲካ፣የኤኮኖሚም ሆነ የሶሻል ሂደት የውጭ አገር መንግስታትና ድርጅቶች እጃቸውን ያላስገቡበት ወቅት አይገኝም።

በነሱ ድጋፍና ፈቃድ የፖለቲካ ስልጣን ይያዛል፣በነሱ ነቀፋና ተቃውሞ የፖለቲካ ስልጣን ይነፈጋል፤በነሱ ፈቃድ የአንድ አገር አንድነት ይጠበቃል፣ በነሱ ግፊትና ድጋፍ አገራት ይገነጣጠላሉ፣ሕዝብም እርስ በራሱ ይተላለቃል።ለሚያካሂዱት ብዝበዛ የሚመች መንግስት ስልጣን ላይ ሲወጣ ለብዝበዛ የማይመቸው አገር ወዳድ ከስልጣን ብቻ ሳይሆን በአካል ይወገዳል።

ለስልጣን ርክክቡ፣ለእርስ በርስ አለመግባባቱ፣ለእራቡና ለድርቁ፣ለበሽታው፣በራስ ድክመትና በተፈጥሮ ጫና ለሚደርሰው አደጋ የውጪ እርዳታና ጣልቃ ገብነት ዋስትና ያለው መፍትሄ ተደርጎ ተወስዷል።በራስ የመተማመኑ ነገር፣ችግርን ተባብሮ የመፍታቱ ፍላጎት እየመነመነ በመሄዱ የታዳጊ አገራት ሕዝቦች ከጥገኝነት ሊላቀቁ አልቻሉም።

ለአንድ አገር ውስጣዊ ችግር የአገሩ ሕዝብ ከሚያቀርበው መፍትሄ ይልቅ የውጪ ሃይሎች ውሳኔና ተሳትፎ የበላይነትና ተሰሚነት አለው።ቡራኬቸውም ግዝተታቸውም የተከበረ ነው።ምንም ጊዜ ቢሆን የታዳጊ በተለይም የአፍሪካ አገሮች ሕዝቦች በራሳችን ወስነንና ፈቅደን ያደረግነው ነገር ቢኖር በጣም ጥቂት ነው።በውጭ ሓይል የቀረበልንን ከመቀበል ሌላ በራስ የመወሰን መብት አልታወቀልንም።እኛም እንዲታወቅልን ያደረግነው ጥረት አነስተኛ ነው።በራሳችን ጉዳይ ላይ እራሳችን እንዳንወስን በዙሪያ ጥምጥም ሰንሰለት ተተብትበናል።ከቶም ለራሳችን ችግር መፍትሄ ለማግኘት የማንችል ድኩማን ተደርገን ተቆጥረናል።በራሳችን ህብረትና እምነት ማጣት፣በጥቂቶች ለግል ጥቅም አጎብድዶ የመኖር ጸባይ የተነሳ ችሎታችን እውቅና አላገኘም።መብታችን ተረግጧል።

እርስ በርሳችን እየተጠራጠርን፣እንዳንስማማ፣ በራሳችን እምነት እንዳያድርብን ሆነናል።

የአገር ተወላጅ ከሚሰጠን መድሃኒት ይልቅ የውጭ አገር ዜጋ የሚሰጠንን መርዝ ለመዋጥ እንሽቀዳደማለን።መልካሙን ነገር ሳይሆን ጎጂውን ባህልና ልማድ በቀላሉ እንቀበላለን።የራሳችን ለሆነው መልካም ነገር ክብርና ዋጋ አንሰጠውም።

ለውጭ አገር መንግስታትና ተቋማት ሎሌ የሆኑ የአገሩ ዜጎች ስልጣን እየጨበጡ የአፍሪካ ሕዝብ ህልውና እዬተደፈረ፣ የተፈጥሮ ሃብቱን እየተበዘበዘ በድህነት እንዲማቅቅ ሆኗል። እራሳቸውን ችለው እንዳይንቀሳቀሱ፣የሕዝብ አንድነት እንዳይኖር ጥገኛ ሆነው እንዲቀሩ በብዙ ግልጽና ስውር ገመዶች ተተብትበዋል።

በውጭ ሃይል የመተማመኑ ነገር በተራው ሕዝብ ዙሪያ ብቻ የሚታይ ድክመት ሳይሆን በምሁሩና በፖለቲካ ፓርቲዎችም ዙሪያ የሚታይ ድክመት ነው።ከሕዝባቸው ይልቅ በውጭ ሃይልና መንግስታት ድጋፍና እርዳታ ስልጣን መያዝን እንደዋና አማራጭና ዋስትና ቆጥረውታል።ከሕዝባቸው ይልቅ የውጭ መንግስታትን ድጋፍና አመኔታን ለማግኘት ያልተቆጠበ ጥረት ሲያደርጉና ሲማጸኑ ይታያሉ።በሁሉም አቅጣጫ የአውሮፓና የአሜሪካን መንግስታት ድጋፍ እንደዋና ተወስዶ በራስ የመተማመኑ ነገር እየመነመነ የጥገኝነትና የባርነት መንፈስ ጠንካራ መሰረት ጥሏል።ለለውጥ ቆመናል የሚሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች ከሕዝባቸው ይልቅ ለከበርቴ አገሮች አምባሳደሮች ምክርና ድጋፍ ትልቅ ከበሬታ አላቸው።ለውጭ አገር ባለስልጣን ልባቸውም ጆሯቸውም ክፍት ነው። አማራጭ ፈረስ ለመሆን እራሳቸውን በበጎ ፈቃድ ሲያቀርቡ ከቶ ሕዝባችን ምን ይለናል አይሉም።መንግስታቱም የነባሩ መንግስት አገልገሎት የማያዋጣቸው ሲሆን ፊታቸውን ወደነዚህ አዲስ መጤ ጉልበተኞች ያዞራሉ፤ለአለፉት ባለስልጣኖች ውለታም በፈጸሙት ወንጀል እንዳይጠየቁ ዋስትናና ከለላ ይሰጡዋቸዋል።

ይህን መሰሉን የባርነትና የበታችነት ሰንሰለት ሁሉም ወዶና ፈቅዶ ተቀብሎታል ማለት አይደለም። ለመበጠስ የሚሹ ቢኖሩም በጸረ ሃይሎች ተንኮልና አመጽ በተግባር ሊገለጽ አልተቻለም።

ለአንድ አገር ብልጽግና፣ ለሕዝቡ ኑሮ መሻሻልና አንድነት ብሎም ለዲሞክራሲ ስርዓት ከራሱ ከሕዝቡ የተሻለ ሚና ሊጫወት የሚችል ሃይል አይኖርም። አገራት እርስ በርሳቸው በጥቅም የተሳሰሩ መሆናቸው ባይካድም፤የሚኖራቸው ግንኙነት በጋራ ጥቅምና መከባበር ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል።የአገራት ግንኙነትና መረዳዳት አስፈላጊነቱ ባይካድም እንደ አጋዥ እንጂ እንደ ዋና መታየት አይኖርበትም።በጌታና በባሪያ መካከልም የሚኖር ግንኙነት ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል።

በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ውስጥ በሚታየው የግንባታና የንግድ የኤኮኖሚ እንቅስቃሴ ከውጭ አገር ከበርቴዎችና ኩባንያዎች እጅ ከተረፈው በተወሰነ ዘርፍ ተወላጁ በተለይም በውጭ አገር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ("ዲያስፖራ" የሚለውን መጠሪያ ለመጠቀም አልሻም፤ምክንያቱን ከዚህ በፊት "ትዝብት" በሚለው ጽሑፍ ትርጉሙንና የቃሉን ታሪካዊ አመጣጥ ያቀረብኩና ለኢትዮጵያኑ ተስማሚ መጠሪያና መታወቂያ አለመሆኑን ስለማምን) የሚያደርገው ተሳትፎ እራስን በመቻሉ ሂደት አስተዋጽኦ ማድረጉ አይካድም።ምንም እንኳን የስርዓቱ አካል የሆነው የቢሮክራሲ ሰንሰለት

በሚፈጥረው ግድግዳና መሰናክል ሳቢያ ፍጥነቱ ቢታገድም፤ያንን በመጋፈጥ ያስመዘገቡት ውጤት የሚናቅ አይደለም።

በፖለቲካውም መስክ፣ ምንም እንኳን ቁጥራቸው ከአስፈላጊ በላይ የሆኑ ድርጅቶች ቢኖሩም፣ሕዝቡን በልዩ ልዩ ጎራ መከፋፈላቸው አደገኛ መሆኑ ባይዘነጋም፤ በተዘዋዋሪ ሕዝቡ ለፖለቲካ ጥያቄ ትኩረት እንዲሰጠው ፣ ንቃተ ህሊናው እንዲጨምር የሕዝብ ተሳትፎ አስፈላጊ እንደሆነ በመጠቆም አኳያ  የሚሰጡት ጥቅም መኖሩ አይካድም። ለጊዜው በተናጠል የሚደርጉት እንቅስቃሴ ከመጨፍለቅ በቀር የትም እንደማያደርሳቸው መረዳታቸው አይቀርም። የማታ ማታ ከተመክሮና በሕዝብ አስገዳጅነት አቋማቸውን ለውጠው ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ከመቆም ሌላ የተሻለ ምርጫ እንደሌላቸው ከወዲሁ ሊያውቁትና ሊቀበሉት ይገባል።በዚህ እረገድ ብዙ ተብሎላቸውና ተጨፍሮላቸው፣ ትዝታ ሆነው የቀሩትን የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ታሪክ ዘወር ብለው ቢመለከቱ ብዙ ሊማሩ ይችላሉ።

በፖለቲካውም ሆነ በኤኮኖሚው እንዲሁም በህብረተሰቡ ባህልና አመለካከት ለውጥ ዙሪያ የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ የተወላጁ ነጻና ቀጥተኛ ተሳትፎ ለአንድ አገር እድገትና ነጻነት ወሳኝ ነው።የበለጸጉ አገራት ሕዝብ ከደረሰበት ደረጃ፣ለሕግ የበላይነትና ለዴሞክራሲ ስርዓት መስፈን  በጎዳናው ያለፉ ፣ልምድ ያዳበሩ የአገሩ ተወላጆች የሚሰጡት ጥቅም ከፍተኛ ነው።የነዚህ ብቃትና የአገር ፍቅር ያላቸው ዜጎች ተሳትፎ የአንድን አገር ሕዝብ በውጭ አገር ሃይልና መንግስታት የመተማመንንና የጥገኝነት ልማድ አሶግዶ እራስን በራስ የመቻልና የመምራት አቅምን ያጎለብታል።የጌታና የባሪያ ግንኙነትን ይሰብራል።

ለዚህ ብሄራዊ ተጋድሎ በውጭ አገር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ በአገር ውስጥ ከሚኖረው ወገኑ ጋር በመተባበር ሊሰራው የሚገባው ታሪካዊና የዜግነት አደራ ይጠብቀዋል።

ለተሻለ ስርዓትና አስተዳደር፣ለዲሞክራሲ መስፈን፣ለህግ የበላይነት፣ለኤኮኖሚ እድገት፣ለሕዝቡ ጤናና ሰላማዊ ኑሮ በሚያረጋግጠው መስክ ብዙ ሊያበረክተው የሚችለው  ሰፊ የተግባር ድርሻ አለበት።ምክንያቱም በሚኖርበት የሰለጠነ ህብረተሰብ ልምዱን ስላካበተ፣ጥቅሙንም ስለተረዳ ለዲሞክራሲ ስርዓት ትልቅ ግምትና አክብሮት አለው። የትውልድ አገሩም በዲሞክራሲ ስርዓት እንድትመራ ፍላጎቱ ከፍተኛ ነው።በሚኖርበት አገር የሰው መብት ሲደፈርና ሲረገጥ ስለማያይ፣እራሱም የዛ ተጠቃሚ ስለሆነ የአገሩ ህዝብም የዛ ጸጋ ባለቤት እንዲሆንለት አጥብቆ ይመኛል።ከአገሩም እርቆ እንዲኖር ያስገደደው ምክንያት በአገሩ የዲሞክራሲ ስርዓት አለመስፈን ስለሆነ ለዲሞክራሲ መከበር የድርሻውን ከማበርከት ወደኋላ አይልም።ምንም እንኳን በፖለቲካው መስክ ተሳትፎ እንዳያደርግ የሚያግደው ሕግና መመሪያ በባለስልጣኖች ቢጸድቅም ፣የዜግነት መብቱን አሳልፎ መስጠት አይኖርበትም።በሀገሩ ውስጥ ገንዘቡን ብቻ ሳይሆን እውቀትና ሃሳቡንም ፣የፖለቲካ እምነቱንም ለማንጸባረቅ የሚያስችለው ዜጋዊ መብት አለው።ለዚህ የዲሞክራሲ ዋና ዋልታ ለሆነው የመብት ጥያቄ ያላሰለሰ ትግል ማድረግ አለበት።ይህን የተራዘመ ትግል የሚጠይቅ ግዙፍ ጉዳይ ለመጀመር የአጭርን የሩቅ የስራ ተሳትፎ ማጤንና ማስላት ግዴታ ነው።

ስለሆነም ለጊዜው አስፈላጊና ቀዳሚ መስሎ የሚታየውና ልንሰለፍበት የሚገባው አንገብጋቢ ተግባር በቅርቡ ለመካሄድ በታሰበው አገር አቀፍ ምርጫ ወቅት በታዛቢነት ለመሳተፍ ፍላጎትን ማሳየትና በተግባር መተርጎም ነው። በተግባር ከተተረጎመ ደግሞ እራስን በራስ የመቻልና በራስ የመተማመን ሂደት የመጀመሪያ የመሰረት ድንጋይ ተጣለ ማለት ነው።

በተለያዩ በሽግግር ላይ ያሉ የአፍሪካና የሌላ አገሮች ውስጥ በሚደረግ ምርጫ ወቅት፣ተሳታፊ ድርጅቶች በሚፈጥሩት ግብ ግብ ፣ገዢው መንግስት በሚወስደው የስልጣን አልነጠቅም ባይነት አሻጥርና ሃይል የሕዝብ ተሳትፎና እምነት ብሎም ሰላማዊ ኑሮ እንደሚናጋ ተደጋግሞ ታይቷል።

ዴሞክራሲ በሌለበት አገር ውስጥ በሚደረግ ምርጫ ግልጽነት የለም፤ግልጽነት ባለመኖሩም መተማመን የለም።አመጽና ውዝግብ አይቀሬ ነው።ምርጫው የይስሙላ ይሆንና ሕዝብን የሚያረካ ውጤት ለማስመዝገብ ያዳግታል።ስለሆነም ሕዝቡን ለተቃውሞ ሰልፍና አመጽ ይጋብዛል።

የቅርብ ጊዜ የምርጫ ታሪካችንን፣ዘወር ብለን ብንመረምር ከላይ ከተገለጸው የተለየና የራቀ አይደለም።

ምርጫ ማካሄድ ማለት ብቻውን የዲሞክራሲን መስፈን አያረጋግጥም።አምባገነን መሪዎችም በነጠላ፣ብቻቸውን ለምርጫ ቀርበው አሸነፍን በማለት የስልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም እንደሚችሉ ባይናችን ያየነውና በጆሯችን የሰማነው ድራማ ነው።አረመኔው መንግስቱ ሀ/ማርያም ሳይቀር በአንድ ወቅት ብቻውን ከራሱ ጋር ተወዳድሮ በ98% ድምጽ ሕዝብ እኔን መርጦኛል ብሎ በድፍረት የተናገረውና የስልጣኑ ባለቤት የሆነበት ኢትዮጵያዊ በሃፍረት የሚያስታውሰው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።የሊቢያውም ሞአመር ጋዳፊ ላለፈው አርባ ዓመት ሙሉ ስልጣኑን የያዙኩት በሕዝብ ምርጫና ውሳኔ ነው ይላል።የኢጅብቱም ሙባረክ እንዲሁ ተቃዋሚውን በግልጽና በስውር እየደፈጠጠ ከሰላሳ ዓመት በላይ በዲሞክራሲ መንገድ የተመረጥኩ ከማለት አልፎ በትረመንግስቱን እንደ ቤተሰብ ቅርስ ለልጁ አሳልፎ ለመስጠት መንገድ እያስተካከለ ነው።የሱዳኑም አልባሽር ያለፈው ሃያ ዓመት ስልጣን አንሶኛል ብሎ በቀጣይነት ለመቆየት በቅርቡ ከራሱ ጋር ለመወዳደር ዝግጅቱን በማጠናቀቅ ላይ ይገኛል። ሌሎቹም የአፍሪካ መሪዎች በተመሳሳይ መልክ ስልጣን አሳልፎ ላለመስጠት የማይገለብጡት ድንጋይ የለም።የአውሮፓና የአሜሪካ መንግስታት በነዚህ አይነቱ መሪዎች ተባባሪነት ጥቅማቸው ስላልተነካ የነዚህን አምባገነን መሪዎች በስልጣን መቆየት ሲደግፉ እንጂ፣በሕዝብ ላይ የሚፈጽሙትን በደል በግልጽ ሲቃወሙና ሲያወግዙ አይሰማም።አልፎ ተርፎም የአፍሪካ ሕዝብ ከበላ ዲሞክራሲ አያስፈልገውም፤ በዲሞክራሲ ተከባብሮና ተሳስቦ መኖር የማይችል አውሬ ነው፤የሚያስፈልገው ሰጥ ለጥ አድርጎ የሚገዛው ጠንካራ መሪ ነው በማለት የጨካኝ መሪዎችን ግፍ ህጋዊ ሽፋን ለመስጠት ይሞክራሉ።የተቃዋሚን ሀይል ለመስበር ድጋፍና እርዳታ እየሰጡ ለይስሙላ በተወሰነ ጊዜ ምርጫ እንዲያካሂዱ ምክር ይለግሷቸዋል።

ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት በነጻና በኩል ደረጃ የማይንቀሳቀስበት፣ድምጹን ለማሰማት የማይችልበት ሁኔታ ባለበት፣ከዛም አልፎ ተርፎ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት አባላት በእስር ቤት በሚታጎሩበትና በሚንገላቱበት አገር ለይስሙላ በሚካሄድ የምርጫ ውድድር ዴሞክራሲያዊ ለውጥ ይመጣል ብሎ መመኘት ከየዋህነት ያለፈ ጅልነት ነው።

በዚህ መልክ የሚካሄድ ምርጫ ስር ነቀል ለውጥ የሚያመጣ ሳይሆን በስልጣን ላይ የተቀመጠ ቡድን በያዘው መንገድ እንዲቀጥልበት "ሕጋዊ" ፈቃድ የሚሰጥ ሂደት ከመሆን  የተለዬ ሌላ ትርጉም አይገኝለትም።

 የዚህ አይነቱ  የምርጫ ሂደት የሚያስከትለው ጣጣ በመንግስትና በሕዝቡ መካከል በሚኖረው  አለመተማመንና የፍላጎት ልዩነት ሳቢያ ግብግብ፣የሰላም መደፍረስና አላግባብ የሰው ደም መፍሰስ ይሆናል።የምርጫ 97ቱ ክስተት ለዚህ ታሪካዊ ማስረጃ ነው።

ዴሞክራሲ በማይከበርበትና ምርጫ እንግዳ በሆነበት አገር በምርጫ ወቅት ሊከሰት የሚችል አደጋ ስለሚታሰብ የውጭ አገር ታዛቢዎች በቦታው እንዲገኙ የማድረጉ ተግባር የተለመደ ነው። ይህም ቢሆን የምርጫውን ዴሞክራሳዊነት የሚያረጋግጥ ሳይሆን የማጭበርበርና የማስገደድ አሰራር መኖሩ ስለሚታመን በሚያስከትለው ውጤት ሳቢያ ሊነሳ የሚችለውን ውዝግብና አደገኛ ክስተት ለማርገብና ለመቀነስ፣በተጨማሪም ለሚፈጠረው ቀውስ ማን ተጠያቂ ፣ማን በዳይ ማን ተበዳይ መሆኑን ለመመስከር ይረዳል ተብሎ ነው።ከሁሉም በላይ ግን የውጭ አገር መንግስታትን ተንኮል የዲሞክራሲ ካባ ለማልበስ የሚያስችል፣ለህዝብ አሳቢና ተቆርቋሪ መስለው የሚቀርቡበት ዘዴ ከመሆን ባሻገር ለሕዝቡ የሚሰጠው ጥቅም የለም።መንግስቱ ሀ/ማርያምንና የመሰሉትን ግፈኛ የአፍሪካ መሪዎች በፈጸሙት የጭፍጨፋ ወንጀልና ግፍ የጠየቃቸው የለም፤እንዲያውም ይባስ ብሎ በነዚሁ የውጭ አገር መንግስታት እርዳታና ቅንብር ነው በሰላም ሊኖሩ የሚችሉበት መንገድ በቅድሚያ የሚዘጋጅላቸው። የውጭ አገር መንግስታት የሚያሳዩት ድርብ ገጽ ለአፍሪካውያን ስውር አይደለም።

የውጭ አገር ታዛቢዎች ተልእኮ በአለፈው የምርጫ ወቅት በአገራችን ተመድቦ ቢረባም ባይረባም ፣የምርጫው ውጤት ያስከተለውን ግርግርና አመጽ ለማቆም ባይችልም የተመደበበትን ግዳጅ አጠናቆ፣ ስለምርጫው የሰበሰበውን መረጃ ለላከው አካል ከማቅረቡም ሌላ ስለምርጫው ሂደት የተገነዘበውን የምስክርነት ቃል በይፋ አውጥቷል።

አሁንም በቅርቡ ይካሄዳል ተብሎ በሚታሰበው ምርጫ ተመሳሳይ የውጭ አገር በተለይም የተባበሩት መንግስታትና የአውሮፓ ፓርላማ የታዛቢ ልኡካን ይመድባሉ ተብሎ ይጠበቃል።

የዚህ አይነቱ ተሳትፎ በአንድ መልኩ ቀና አስተዋጽኦ ቢመስልም በሌላው ገጹ በአንድ አገር ጉዳይ ሕዝቡ ሊኖረው የሚገባውን ድርሻና ሓላፊነት እንዳይወጣ፣የራሱን ችግር በራሱ እንዳይፈታ፣ከራሱ ዜጋ ይልቅ በይበልጥ በውጭ ዜጋ እንዲተማመን፣የጥገኝነትና የበታችነት ስሜት እንዲቀጥል ይረዳል የሚል ስጋት ያሳድራል።

እርግጥ ኢትዮጵያውያን በባህላችን የለመድነውና ያሳደግነው የእርስ በርስ ውስጣዊ ችግር አፈታት ዘዴ አለን።እኛው መርምረንና ተከታትለን ተገቢ ፍርድ ልንሰጥበት የሚያስችል ልምድና ችሎታ አዳብረናል።ችግር ሲከሰት፣የወንጀል ስራ ሲፈጸም ምንጩን ለማወቅ በመከታተል፣በአውጫጭኝ/በአፈርሳታ/፤በሰዎች መካከል ጠብና ግጭት ሲነሳ ወደ ባሰ ችግርና ደም መቃባት እንዳያመሩ በቤተሰብ ዳኛ፣በአገር ሽማግሌ፣ በቃዲ ጉባኤና በሃይማኖት አባቶች እርቅ እንዲወርድና የበደለ ጉማ /ካሳ/ እንዲከፍል የማስገደድና ዳኝነት የመስጠት ችሎታ ከጥንት ጀምሮ የተለመደ፣ እንግዳና ባዳ ያልሆነ  አሰራር ነው።ለውስጥ የርስ በርስ አለመግባባትና ግጭት እንኳንስ አሁን ዘመናዊ የህግ አሰራር ባለበትና በተለመደበት ጊዜ ቀርቶ በጥንቱም ጊዜ ቢሆን ችግሮች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ የሚያስችል ጥበብና እውቀት አለን።ስለሆነም ፍላጎቱና ድፍረቱ ካለን እራሳችንን ችለን ለዳኝነቱም ሆነ ለምስክርነቱ የማንበቃበት ምክንያት የለም።ድፍረቱ ካለን ፣አንድነቱና ፍላጎቱ ካለን የማንወጣውና የማናቃልለው ችግር አይኖርም።

ችግርን ለመፈታት ብልሃቱ አለን ብንልም፣ እስካሁን ድረስ በፖለቲካ ዙሪያ ከጉልበትና ከጠመንጃ የተለዩ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ዘዴ አልተጠቀምንም። ብንሞክርም።የዴሞክራሲ አሰራር እንዳይሰፍን በሚከላከሉ ሃይሎች አመጻዊ እርምጃ በተግባር ላይ እንዳይውል ተደርጓል።ይህ ኋላ ቀር ኢዴሞክራሲያዊ ልማድና አሰራር ከጊዜው ጋር ስለማይሄድ የግድ መልኩን መቀየር ይኖርበታል።በዱላና በሽብር ስልጣን የመያዙ ልማድ በሕዝቦች ውሳኔና ምርጫ መተካት አለበት።ለዚህ እራስን ለመቻልና ለዲሞክራሲ መከበር ለሚያበቃ ሰላማዊ ትግል ፍላጎት ያለው ወገን የሚችለውን አስተዋጽኦ ለማበርከት በሚችልበት መድረክ መሰለፍ ይኖርበታል።

እራስን የመቻሉን ሂደት በተግባር ለመተርጎም ከሚያስችለው  አንዱ የቅርብ ጊዜ ተግባር እስከ አሁን ድረስ የውጭ አገር ዜጎች የሚሳተፉበት የምርጫ ወቅት ታዛቢ ቡድን ስራ በተወላጁ የሚተካበትን ሁኔታ መፍጠር ነው።

ለአገር ጉዳይና ለሚገጥም ችግር እራሳችን መፍትሄ መሆን እንደምንችል ካመንበት፤ ፍላጎቱና ድፍረቱ ካለን ለውጭ አገር መንግስታትና ሃይሎች አሳልፈን የምንሰጠውን ሃላፊነት እራሳችን መውሰድ ይኖርብናል። ይህንን ለማድረግ ከቻልን አላስፈላጊ ጥገኝነትን በማሶገድ እራስን በራስ የመቻሉንና በራስ የመመካቱን ባህል መሰረት ጣልን ማለት ነው።የጌታና የባሪያ ግንኙነትን ሰንሰለት ለመበጠስ የምንችለው በራሳችን ስንተማመንና እርስ በርስ ስንከባበር ነው።የውጭ ታዛቢዎች ከሚሰጡት ፍርድና የምስክር ቃል ይበልጥ በአገሩ ተወልዶ ያደገው ባህሉን፣ቋንቋውን፣ ሕብረተሰቡንና ከባቢውን የሚያውቀው፣ለግል ጥቅም ያላደረ ዜጋ የሚሰጠው ፍርድና አስተያየት በሕዝቡ ዘንድ ይበልጥ ተቀባይነት ይኖረዋል።የኔነትንም ስሜት ያሳድራል።

ያገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ ነውና አገራችን የሚገጥማትን ችግር ለማሶገድ በቅድሚያ እኛ ተወላጆቹ ሃላፊነቱን መውሰድ ይኖርበታል።

የጽሁፉ አንባቢዎች የመልዕክቱን ፍሬ ነገር በቀና መንፈስ እንደሚመለከቱትና ጥሪውን ተቀብለው በተግባር እንደሚተረጉሙት ተስፋ አለኝ።የተለዩና የተሻለ ሃሳብም ካል ከመቀበል ወደኋላ አልልም።

ጥሪውን ተቀብላችሁ በተግባር ለመሰማራት የምትሹ ሁሉ አስተያየታችሁን በአስቸኳይ ብትገልጹ በቀረን የሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ የሚያስፈልገውን ዝግጅት ለማጠናቀቅ ይረዳናል።ለዚህ ብሄራዊ የወዶ ዘማች ተሳትፎ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላትና የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች፣በተለይም ምርጫውን በአላፊነት የሚመራው የምርጫ ቦርድ ቀና አመለካከት እንደሚኖራቸውና የሚያስፈልገውን ትብብር እንደሚያደርጉ ተስፋ እናደርጋለን።ጥቅሙ ለሁሉም ነው።

በተጨማሪም በዚህ የኢትዮጵያውያን የምርጫ ታዛቢ ቡድን ውስጥ ለመካፈል የሚፈልግ ግለሰብ የሚያስፈልገውን የመጓጓዣም ሆነ የመሰንበቻ ወጭ እራሱ መሸፈን እንደሚኖርበት በቅድሚያ ሊያውቀው ይገባል።**እራስን በራስ** ከዚህ ይጀመራል።

ከሰላምታ ጋር

አስተያየታችሁንም ሆነ ለመካፈል ያላችሁን ፍላጎት፣ስምና አድራሻ ጭምር በሚቀጥለው የመልክት አድራሻ ልትልኩ ትችላላችሁ

a.addis@quicknet.nl